በመ/ገ/ጽ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰ/ት/ቤት ትምህርት ክፍል የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መልመጃ

1. “ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክቶች ለአንተ አይሁንልህ” የሚለው የመጀመሪያው ትዕዛዝ ምን ያስገነዝበናል? በተማራችሁት መሰረት መልሱ

2. “የተቀረጸ ምስል ለአንተ አታድርግ” የሚለውን ትዕዛዝ መሰረት አድርገው ታቦትና ቅዱሳት ስዕላት አያስፈልጉም ለሚሉት የእርሰዎ ምላሽ ምንድ ነው?

3. እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ እንዳንጠራ የከለከለን ለምንድ ነው? ስሙን በከንቱ ጠርተናል የሚያሰኙ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

4. ሰንበትን የምናከብረው ለምንድ ነው? በቅድሥት ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት በዓላት እንዴት መከበር ይገባቸዋል? በዓላት አያስፈልጉም ለሚሉ ሰዎች የእርሰዎ ምላሽ ምንድ ነው?

5. ወላጆችን ማክበር የሚገባው ለምንድ ነው? ወላጆችን ማክበር በምን መንገድ መገለጽ ይኖርበታል?

6. አትግደል የሚለው ትዕዛዝ የተሰጠው ለምንድ ነው? በተማራችሁት መሠረት ስንት አይነት መግደል አለ? እነ ማን ይባላሉ?

7. አንድ ሰው አመንዝራ ነው የምንለው ምን ሲያደርግ ነው? አመንዝራነት የሚያስከትለው ጉዳት ምንድ ነው?

8. ወደ ዝሙት ኃጢአት የሚገፉፋ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ከዝሙት ኃጢአት ለመጠበቅ ምን ማድረግ ይገባል?

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር

✍ ቴዎድሮስ ዘውዱ